**אמהרית**

## የ18ኛው ክኔሴት
## ማዕከላዊ የምርጫ ኮሚቴ

## የእስራኤል የምርጫ ሥርዓቶች
## የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ የመረጃ ወረቀት

የእስራኤል ክኔሴት ምርጫ የሚከተሉት ጠባያት አሉት።

አጠቃላይ — ማንኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ የአገሪቱ ዜጋ በምርጫዎች ላይ የመሳተፍ መብት አለው።

ብሔራዊ — የምርጫዎቹን ውጤቶች ለማስላት ያስችል ዘንድ መላው እስራኤል እንደ አንድ የምርጫ ክልል ተደርጎ ይታያል።

ቀጥተኛ — ተመራጮች የሚወሰኑት በቀጥታ ድምጽ አሰጣጥ መሠረት ነው (በተዘዋዋሪ የምርጫ ስልት ሕዝቡ መራጭ አካል የሚመርጥ ሲሆን ያ መራጭ አካል ደግሞ ተሿሚዎችን ይመርጣል። የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ምርጫ ጥሩ ምሳሌ ነው)።

እኩል የሆነ — እያንዳንዱ መራጭ አንድ ድምጽ አለው። ሁሉም መራጮች ምርጫው ላይ ተጽእኖ ለማሳደር እኩል ኃይል አላቸው።

ምስጢራዊ — ድምጽ አሰጣጡ ምስጢራዊ ነው። ድምጽ እንዴት አድርጎ እንደተሰጠ ከመራጩ ውጪ የሚያውቅ ሰው የለም። የድምጽ አሰጣጡን ምስጢራዊ የሚያደርጉት ነገሮች

- የታሸገ የድምጽ መስጫ ፖስታ። ይህ ፖስታ በውስጡ ምን ዓይነት ወረቀት እንደተቀመጠበት ለማየት አያስችልም።
- የድምጽ መስጫው ቦታ የተከለለ ሲሆን መራጩ የምርጫውን ወረቀት ፖስታው ውስጥ በሚከትበት ጊዜ ሌላ ሰው እንዳያየው ይሸፍነዋል።

*መራጩ በፈለገው ዓይነት ድምጽ መስጠት የሚችል ሲሆን እንዴት አድርጎ እንደመረጠ ሌላው ሰው ሊያውቅ አይችልም።*

ልብ በሉ፡ — ምርጫዎች የሚካሄዱት ሽቫት 16 ቀን 5769 ዓ.ዓ. ወይም የካቲት 10 2009 ዓ.ም. ነው።

# אמהרית

## <u>የምርጫ ውጤቶች</u>

1. ከተጣሩት ድምጾች ክፍፍል ቢያንስ 2% የተቀበሉ ማንኛቸውም ፓርቲዎች በማንዳት (מנדט) ክፍፍል ላይ ይሳተፋሉ።
2. በክፍፍሉ ላይ የሚሳተፉት ፓርቲዎች የተጣሩ ድምጾች ለ120 የሚካፈል ሲሆን በማካፈል የሚገኘው ውጤት ቁጥር “መለኪያ” (מודד) ይሆናል።
3. ሁሉም ፓርቲ የሚያመጣው ድምጽ በመለኪያው ውጤት ከተከፋፈለ በኋላ ተገቢውን የማንዳት (מנדט) ቁጥር ያሸንፋል

## <u>የመራጮች መዝገብ ላይ የሚመዘገበው ማን ነው?</u>

የመራጮች መዝገብ የሚባለው ለክኔሴት የምርጫ መብት ያላቸውን ሰዎች ስም የያዘ መዝገብ ነው።

በ18ኛው የክኔሴት ምርጫ ላይ በመራጮች መዝገብ ላይ ለመመዝገብ መብት የሚኖራቸው የሚከተሉትን 3 ነገሮችን የሚያሟሉ ናቸው።

- ❖ ከ18.2.2008 በፊት የእስራኤል ዜጋ የሆነ
- ❖ ከ10.2.1991 በፊት የተወለደ
- ❖ ስሙና አድራሻው ከ18.12.2008 በፊት በሕዝብ መዝገብ ተመዝግቦ የሚገኝ

የመራጮች መዝገብ የምርጫ ቦታን ለማወቅ እንዲያስችል በኢንቴርኔት ድረ ገጽ ላይ ይቀርባል። መዝገቡ <u>www.gov.il</u> በተባለው ድረ ገጽ ላይ ይቀርባል።
መዝገቡ ግልጽ የሚሆንበት ጊዜ በተገቢው ወቅት የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ድረ ገጽ በሆነው በ<u>www.bechirot.gov.i</u> ላይ ይቀርባል።

## <u>ድምጽ የሚሰጠው የት ነው?</u>

❖ በምርጫው ቀንና ምርጫው ከመደረጉ በፊት የድምጽ መስጫው ትክክለኛ ቦታ የት እንደሆነ በማዕከላዊው የምርጫ ኮሚቴ ቴሌፎናዊ የመረጃ (ኢንፎርሜሽን) ቢሮ አማካይነት ማጣራት ይቻላል። የስልክ ቁጥሮቹም በጋዜጣ ላይ ይታተማሉ።

❖ የአካላዊ እንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው ሰዎች የአካላዊ እንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው ሰዎች ተብለው በተዘጋጁ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ድምጽ መስጠት ይችላሉ። ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ ቢሮዎች አማካይነት የአካላዊ እንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው ሰዎች የትኞቹ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አመቺ እንደሆኑ ማጣራት ይቻላል።

❖ እንደዚሁም በሆስፒታሎች፣ እስር ቤቶች፣ የእስራኤል መርከቦችና ውጪ አገር በሚገኙ የእስራኤል ወኪል መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ድምጽ ይሰጣል።

❖ ከምርጫው 3 ሳምንት አስቀድሞ ለእያንዳንዱ መራጭ የት ድምጽ እንደሚሰጥ ትክክለኛው የቦታው አድራሻ ይላክለታል። የድምጽ መስጫውን ቦታ ካርታ <u>www.gov.il</u> በተባለው ድረ ገጽ ላይ ማየት ይቻላል።

# אמהרית

## የምርጫው ቀን

የምርጫው ቀን ሥራ የማይሠራበት ቀን ነው። ቢሆንም ግን የሕዝብ ማመላለሻዎች በተለምዶው ዓይነት ይሠራሉ። በምርጫው ቀን የድምጽ መስጫ ቦታዎች ከጧቱ 7 ሰዓት እስከ ምሽቱ 10 ክፍት ናቸው። (በትናንሽ መንደሮችና የመራጮቹ ቁጥር ከ350 የማይበልጥ ከሆነ ድምጽ የሚሰጠው ከጧቱ 8 እስከ ምሽቱ 8 ሰዓት ድረስ ነው።) የድምጽ መስጫዎቹ ቦታዎች በሮች ልክ ከምሽቱ በ10 ሰዓት ላይ ይዘጋሉ (በትንንሽ መንደሮች በ8 ሰዓት)። ድምጽ ለመስጠት ሰልፍ ላይ ያሉ ሰዎች ድምጽ እንዲሰጡ ይፈቀድላቸዋል። ነገር ግን ቦታው ከተዘጋ በኋላ ወደ ድምጽ መስጫው ቦታ የሚመጣ ሰው ድምጽ መስጠት አይችልም።

ድምጽ የሚሰጠውን ሰው በሚከተሉት ዓይነት መንገዶች መለየት ይቻላል።:

- የድምጽ ሰጪው ፎቶ ያለበት መታወቂያ ወረቀት.
- የድምጽ ሰጪው ፎቶ ያለበት የእስራኤል ፓስፖርት.
- የድምጽ ሰጪው ፎቶ ያለበት የእስራኤል መንጃ ፈቃድ.
- የክኔሴት አባል መታወቂያ.

## የድምጽ መስጫ ሳጥንና የተከለለ የድምጽ መስጫ ቦታ

የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች የሚከተሉት ናቸው።

- መራጩ ለአስመራጩ ኮሚቴ ፀሐፊ ራሱን በመታወቂያ ወረቀት አማካይነት ያስተዋውቃል።

- መራጩ ስሙ በመራጮች መዝገብ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ “የ18ኛው ክኔሴት ምርጫ” ተብሎ የተጻፈበትና ሰማያዊ ቀለም ያለው የምርጫ ፖስታ ይቀበላል። የድምጽ መስጫ ፖስታዎች የተዘጉና ከውስጥ የጠቆሩ ሲሆን የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴና የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ማኅተም አለባቸው። እንደዚሁም የአስመራጩ ኮሚቴ 2 አባላት የእጅ ፊርማም አለባቸው።

- መራጩ ወደ ድምጽ መስጫው የተከለለ ቦታ ውስጥ ይገባል። ከፊት ለፊቱም ለክኔሴት ዕጩ የሆኑ ፓርቲዎች ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ተቀምጠው ያገኛል። እንደዚሁም ነጭና ባዶ ድምጽ መስጫ ወረቀቶችም ይገኛሉ።

**אמהרית**

## <u>የክኔሴት ድምጽ መስጫ ወረቀት — ለሁሉም ፓርቲዎች</u>

ድምጽ የሚሰጠው ለፓርቲዎች ነው። በያንዳንዱ ድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ የፓርቲው ስምና የሚወክለው ፊደል ወይም ፊደላት ተጽፈዋል። የፓርቲዎች ስም (መጠሪያ) እና ፊደላቶቻቸው በጋዜጣ ላይ ይታተማሉ።

**ድምጽ የሚሰጠው በሚከተለው መንገድ ነው**

- ድምጽ ሰጪው እሱ ሊመርጠው የሚፈልገው ፓርቲ ስምና ፊደል ያለበት አንድ የድምጽ መስጫ ወረቀት ብቻ ይመርጣል። ከዚያም ያንን ወረቀት በክኔሴት ምርጫ ፖስታ ውስጥ ይከተዋል። መራጩ ፖስታውን መዝጋት አለበት። መራጩ ከፈለገ በነጭና ባዶ የድምጽ መስጫ ወረቀትም መጠቀም ይቻላል። በዚያም ወረቀት ላይ የሚመርጠውን ፓርቲ ፊደልና ስም ይጽፋል (መጻፍ የሚችለው በዕብራይስጥ ወይም በዓረብኛ ብቻ ነው)።

- መራጩ ከተከለለው ቦታ ውስጥ በመውጣትና በእጁ የታሸገውን ፖስታ በመያዝ ወደ ድምጽ መስጫ ሳጥን በመቅረብ የኮሚቴው አባላት እያዩት ፖስታውን ወደ ድምጽ መስጫ ሳጥን በገዛ እጁ ይከትታል።

- መራጩ የሥነ ሥርዓት አስከባሪዎቹን ትእዛዝ መስማት አለበት።

ለምርጫው ፖስታ አንድ የድምጽ መስጫ ወረቀት ብቻ መከተት ያስፈልጋል። በአንድ ፖስታ ውስጥ ሁለት የአንድ ፓርቲ ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ቢገኙ ድምጹ አይሰረዝም (ነገር ግን አንድ ወረቀት ብቻ ነው ከግምት የሚገባው)። ነገር ግን በፖስታው ውስጥ ከ2 በላይ የአንድ ፓርቲ ድምጽ ወረቀቶች ወይም የተለያዩ ፓርቲዎች ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ቢገኙ ድምጹ ይሰረዛል።

የመጀመሪያው (ኦሪጂናል) የዕብራይስጥ ጽሑፍ
**የ18ኛው ክኔሴት**
**ማዕከላዊ የምርጫ ኮሚቴ**
www.bechirot.gov.il

“የ18ኛው ክኔሴት ምርጫ” መረጃ ወረቀት የአማርኛ ትርጉም
ለአዲስ ገቢዎች አገልግሎት ተብሎ የተዘጋጀ
**የአዲስ ገቢዎች ማስተናገጃ መሥሪያ ቤት፣ የኅትመት ክፍል**
www.moia.gov.il

**ኢየሩሳሌም 2008 / 2009 - መብቱ የተጠበቀ ነው - ©**